በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY

የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

# የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት 228/07

ቀን: 30/10/07 ዓ.ም

ለ: ም/ስራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች/
ም/ስራ አስኪያጅ /የሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/
ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የሥራ ሂደት
ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
ህግ ማስከበር የሥራ ሂደት
አቃቤ ህግ የሥራ ሂደት
ድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት
ገላን ኮንቴይነር ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ
ውስጥ ኦዲት ቡድን
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

ከ: ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ በደብዳቤ ቁጥር 3.0/223/07 ቀን ሰኔ 24/2007 ዓ.ም. በ2012 የታሪፍ መጽሐፍ መሠረት በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ የታሪፍ ማተካከያ ያልተደረገበት ዕቃን በተመለከተ በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ ያልተስተካከለውን የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ እንዲያስተካክልና በኤክሳይስ ታክሱ ላይ ማስተካከያ ባለመደረጉ ምክንያት በታሪፍ ቁጥር 8528.6900 በሚመደቡ ፕሮጀክተሮች ላይ በአንደኛ መደብ 30% የጉምሩክ ቀረጥ እየተከፈለ ያለው በ2012 ቨርዥን ታሪፍ ማሻሻያ መሠረት 10% ሆኖ ማስተካከያ እንዲደረግበትና ተግባራዊ እንዲሆን ገልፆ ጽፎልናል፡፡

በመሆኑም በማስተካከያ ውሳኔው መሠረት ይፈፀም ዘንድ እያሳሰብኩ፤ የደብዳቤው ኮፒ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር የተላከላችሁ መሆኑን እገልፃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

መ/አ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ለመረጃና ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

የጉምሩክ ስነ ስርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ቁጥር / Ref. No 3.0/723/07

ቀን / Date 24/10/07

ጉዳዩ:- በ2012 የታሪፍ መጽሃፍ መሰረት በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ የታሪፍ ማስተካከያ ያልተደረገት እቃን ይመለከታል፤

የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥ 07.02/107/07 በቀን ሚያዝያ 05/2007 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ የ2012 እትም (ቨርዥን) የታሪፍ መጽሃፍ ከጥር 1/2006 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የተላለፈ ቢሆንም በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ ማስተካከያ እንዳልተደረገ በመግለጽ በተለይ በፕሮጀክተሮች ላይ የተደረገው ማሻሻያ ባለመስተካከሉ ለማስተናገድ መቸገራቸውን በመግለጽ መፍተሄ እንዲሰጥበት መጠየቃቸው ይታወሳል::

ከዚህም በተጨማሪ በቁጥር መቴስ/9759/07 በ15/4/07 ከመረጃና ቴክኖሎጅ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተጻፈ ደብዳቤ በ2007 ቨርዥን የታሪፍ መጸሃፍ ላይ የታሪፍ ቁጥር 8528.6900 በአሲኩዳ++ ሲስተም የጉምሩክ ቀረጥ በአንደኛ መደብ 30%፣ ኤክሳይስ ታክስ 10% ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን ጠቅሰው ነገር ግን በ2012 ቨርዥን የታሪፍ መጽሃፍ ደግሞ በአንደኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ 10% እና ኤክሳይስ ታክስ ግን የሌለው መሆኑን በመግለጽ በዚሁ ጉዳይ ላይ የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬትን ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ዳይሬክቶሬቱ በቁጥር 3.1.0/2007/07 የካቲት 18/2007 በጻፈው ደብዳቤ በ2007 ቨርዥንም ሆነ በ2012 ቨርዥን የታሪፍ መጽሃፍ ላይ ኤክሳይስ ታክስ ምልክት(+) እንዳልተደረገበትና የታሪፍ ቁጥር 8528.6900ን በተመለከተ 10% ኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበት መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ ወይም መመሪያ በዳይሬክቶሬቱ በኩል የተላለፈ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩን በመጥቀስ ነገር ግን በሌላ ወገን በኩል በተላለፈ መመሪያ ወይም ደንብ ኤክሳይስ ታክስ እንዲከፈልበት ተደረጎ በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ እንዲገባ ተደርጎ ከሆነ በመረጃና ቴክኖሎጅ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በኩል ተጣርቶ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻል መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ቢጽፍም መረጃ ማግኘት ስላልተቻለ የታሪፍ ቁጥር 8528.6900 ላይ በ2012 ቨርዥን የታሪፍ መጽሃፍ መሰረት በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ ማስተካካያ ያልተደረገ በመሆኑ በአሰራር ላይ ችግር ስለፈጠረ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

እልባት ለመስጠት ከባለስልጣን መ/ቤታችን የተለያዩ ዳይሬክቶሬቶችና ቅ/ጽ/ቤቶች በተውጣጡ ባለሞያዎችና ሀላፊዎች ጋር በ12/10/2007 በጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ ዳ/ር ቢሮ በተደረገ ዉይይት የኤክሳይስ ታክስ አዋጁ ከወጣ በኋላ በፕሮጀክተሮች ላይ የኤክሳይስ ታክስ ለመጣል ማሻሻያ የተደረገ ስለመሆኑ አዋጅና ደንብ ወይም መመሪያ ካለ ተረጋግጦ የሕግ አስተያየት እንድሰጥበት በተደረገዉ ስምምነት መሰረት የሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት በውስጥ ማስታወሻ ቁጥር ሕ/ም/አ/ዳ/194/07 በቀን 16/10/07 አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም ተያይዞ በተላከዉ ሁለት ገጽ ኮፒ የሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት አስተያየት መሰረት የመረጃና ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ፕሮጀክተሮችን በተመለከተ በአሲኩዳ++ ሲስተም ዉስጥ ያልተስተካከለውን የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ እንዲያስተካከልና በኤክሳይስ ታክሱ ላይ ማስተካከያ ባለመደረጉ ምክንያት በታሪፍ ቁጥር 8528.6900 በሚመደቡ ፕሮጀክተሮች ላይ በአንደኛ መደብ 30% የጉምሩክ ቀረጥ እየተከፈለ ያለዉ በ2012 ቨርዥን ታሪፍ ማሻሻያ መሰረት 10% ሆኖ ማስተካከያ እንዲደረግበትና ተግባራዊ እንዲሆን አሳስባለሁ፡፡

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር በኩልም ጉዳዩን በተመለከተ ከባለስልጠን መ/ቤታችን የሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት በተሰጠዉ አስተያየት መሰረት ተግባራዊ እያደረግን ስለሆነ ኮፒዉ ተያይዞ በተላከዉ የሕግ አስተያየት ላይ የተለየ አቋም ካለ በስቸኳይ እንድናዉቀዉ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ካይላኢ ገዛኸኝ
ም/ዋና ዳይሬክተር
የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና
ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

<u>ግልባጭ</u>

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አ/ፕ/ል/ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች ቅ/ጽ/ቤት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-እቃ አወጣጥ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባ አ/ፕ/ል/ቡድን

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

<u>አድስ አበባ</u>

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
የዐቃቤ ህግ ቢሮ የህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
Prosecution Office Legal Advice and Opinion Directorate
የህግ ምክርና አስተያየት ማስታወሻ
Memorandum of Legal Advice and Opinion

ለ፡ ዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት — ቀን፡16/10/07

ከ፡ ሕግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት — ቁጥር፡ ሕ/ም/አ/ዳ/194/07

ጉዳዩ፡- <u>በፕሮጀክተር ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈልን በተመለከተ</u>

## የጉዳዩ ፍሬ ነገር

በ2007ም ሆነ በ2012 በወጣው የታሪፍ መጽሀፍ ላይ እንዲሁም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 መሠረት ወደ ሀገር በሚገቡ ፕሮጀክተሮች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ እንደሚከፈል ባያመላክትም ነገር ግን በአሲኩዳ ሲስተም ውስጥ በዚህ እቃ ላይ 10% ታክስ የተጣለ እና ታክሱ እየተሰበሰበ በመሆኑ የዚህን መነሻ ለማጣራት በተደረገው ስብሰባ ታክሱ የተጣለበት የህግ መነሻ ያልተገኘ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንድንሰጥበት ጥያቄ ቀርቧል።

## የጉዳዩ ጭብጥ

ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ፕሮጀክተሮች ላይ ኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል የሚያደርግ ህግ አለ?

## አግባብነት ያለው ህግ

- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 570/2000
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 610/2001

## የህግ አስተያየት

የኤክሳይዝ ታክስ በቅንጦት ዕቃዎች እና መሠረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ፍላጐታቸው በማይቀንስ እቃዎች ላይ የሚጣል ታክስ ሲሆን ታክሱ የሚጣልባቸው እቃዎች ዝርዝር እና የታክሱ መጠን በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ላይ በተያያዘው ሠንጠረዥ ተለይተው ተመልክተዋል። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ፕሮጀክተር ታክሱ ከሚጣልባቸው እቃዎች ውስጥ ያልተካተተ ከመሆኑም በላይ ዕቃው ከላይ

የተገለፀው የዕቃ ባህሪ የሌለው በመሆኑ በዚህ ዕቃ ላይ ታክሱን ለመጣል ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ምክንያት የለም። በዚህ ምክንያት በ2000 እና በ2001 ዓ.ም በኤክሳይዝ አዋጅ ላይ በተደረጉት ማሻሻያዎች ላይም በፕሮጀክተር ላይ ታክሱን ለማስከፈል የተደረገ ማሻሻያ የለም።

በመሆኑም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ እና በተደረጉት ማሻሻያዎች ላይ ፕሮጀክተር ታክሱ ከተጣለባቸው እቃዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ ዕቃው ወደ ሀገር ሲገባ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት አለመሆኑን በመግለጽ አስተያየታችንን እናቀርባለን።

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>

- ለዐቃቤ ህግ ቢሮ
  <u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. ፪
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2